ቀን ሰኔ 6 ቀን 2013 ዓ.ም

ለዶክተር ምስጋነዉ አንዷዓለም ወይ መማር!

የጻፉትን 281 ገጽ መጽሐፍ ሳነብ የአገኘሁትን አላስፈላጊ ሐሳቦች በመንቀስ ችግሮችን ስጠቅስ በአእምሮዎት ስለዉ የአስቀመጡትን ምስል ከመሆን ለመመለስ ሳይሆን፣ ለእባቢያን ዳኝነት ለመስጠት እንዲችሉ ያመቻቸው ዘንድ ነዉ፡፡

«ጊዮናዊ አማራ» ሲሉ በሰየሙት መጽሐፊዎ ገጽ 94 ላይ «ሞረሽ እንደሲቪክ ድርጅት ቢንቀሳቀስም፣ አማራን የማደራጀት ስራ እየራ አልነበረም» ብለዋል ፡፡ ሐቁ ግን ፣ሞረሽ ማንም ሰዉ እራሱን ዐማራነኝ ማለት በፈራበት ዘመን ከመስከረም 2005 ዓ.ም ጀምሮ የዐማራን መበደል ከ500 በላይ በሆኑ መግለጫዎች፣በፓልቶክ፣ በራዲዮና በቴሌቪዥ፣ በሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ በስፖርት ሜዳዎች ወዘተ ዐማራው ዐማራ ነኝ ብሎ እንዲደራጅና ከዘር እልቂት እንዲከላከል፣ የቀሰቀሰ፣ ያስተማረና ያደራጀ የሲቪክ ድርጅት መሆኑን ዓለም ያውቀዋል። በትግሬ ወያኔ ዘረኛ አመራር በዐማራው ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ዓለም አቀፍ ወንጀል አስጠንቶ፣በአገር በአራት ዓይነት ቋንቋዎች አስተርጉሞ ለዓላም ማኅበረሰብ፣ ለሰባዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና ለራሱ ለዐማራው ሕዝብ ያቀረበ የተግባር ድርጅት ነው። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ትውልዱም ሆነ የዓለም ማኅበረሰብ ድርጊቱን እንዳይረሳ፣ «ምጽአተ ዐማራ፤ ተገድሎና ተገዳድሎ የማያልቅ፣ ተነቅሎ የማይደርቅ» በሚል ርይስ በ657 ገጽ ሰንዶ ለንባብ ያበቃ ድርጅት ነው። የዐማራው ልሳን የሆነ «የዐማራ ድምፅ ራዲዮ» የተሰኘ የአጭር ሞገድና የኢንተርኔት ራዲዮ ከፍቶ ዐማራውን በማንቃትና በማደራጀት ላይ ያለ ድርጅት ነው። ይህ የሚክድ ካለ የዐማራው ጠላት የሆነው ወያኔ ብቻ ነው።

በዚሁ 94 ገጽ ላይ «ሞረሽ አለመስራቱ ብቻ አይደለም፣ የሚሰሩትን ጠልፎ የሚታገል በመሆኑ የችግራችን አካል ነበር» ብለዋል፡፡እርስዎ አቶ በነበሩበት ጊዜ እነ መሳፍንት ባዘዘዉ አቋቋሙት የአሉትን አወጋንን ከሃሳብ እስከ ገንዘብ እርዳታ ማድረጉ ጠልፎ መጣያ አድርገዉ የአዩት የሚመስለኝ አሁን ዶክተር ከሆኑ በኋላ በረቀቀ አስተሳሰብዎ አቅለዉት ካልሆነ በስተቀር ሞረሽማ ለአወጋን መጠንከር የሚችለውን ሁሉ ያደረገ ነው፡፡ አሜሪካ የአወጋን ተጠሪ የነበረውን ግለሰብ ዲሲ ውስጥ ሕዝባዊ ስብሰባ በመጥራት ዓላማውን ገልጾ፣ መንቀሳቀሻ ድጋፍ እንዲያገኝ አድርጓል። በጥሬ ገንብ እርዳታ ያደረገ ነው። ይህን አቶ መሳፍንት ባዘዘው የሚከደው አይሆንም። ይህን እርስዎ ቢክዱት፣ የአወጋን መሪዎች እና ለእርዳታ የተሰበሰቡት አባላት ሃሳብዎትን በሀሰትነት እንዳያዩብዎት አስጋለሁ፡፡

ዶክተር በመጽሐፍዎት 94 ገጽ ላይ « በአማራነት መበደሉን የሚያምን ጥቂት ህዝብ ቢኖርም እንዲደራጅ ጥሪ ይደረግለት የነበረዉ በኢትዮጵያዊነት ነዉ» ሲሉ አጥብቀዎ እና ደጋግመዉ ይኮንናሉ፡፡ የእርስዎ ድርጅት መነሻዉ አማራ ሲሆን መድረሻዉም የአባት ሀገር አማራ እንደነበር እና በዚህ አደረጃጀታችሁ ከሞረሽ ጋርም እንደስዎ አመለካከት ግጭት ሳይሆን የሃሳብ አንድነት እንዳልነበረ የአባት ሀገር እና መገንጠል ትሉት በነበረዉ ሃሳብ ብዙ ዉይይት እንዳደረግንበት እና አባሎቻችሁም በሁለት አስተሳሰብ ተከፍላችሁ እንደነበርን እናዉቃለን፡፡ ይህ ሊሆን የቻለዉም በዉይይት እና በሃሳብ አሸናፊነት እንደሆነ ሁሉን አዋቂና ፍጹም ለሆኑት ዘመናዊ ዶክተር ይሳነወታል ስለማልል በዚሁ አልፈዋለሁ፡፡

«ቤተ-ዐማራ ካልጠፋልኝ የሚለዉን ሞረሽ እና ቤተአማራን ለምን? አንድ አትሆኑም እያሉ አይናችሁ ለአፈር ይሉናል» ብለዋል፡፡ ሞረሽ ቤተዐማራ ካልጠፋ ማለት ቀርቶ በእርስዎ ፓልቶክ እና በስልክ ቁጥርዎት 5093394721 ከአቶ ጋሻዉ ጋር በስልክ ቁጥራቸዉ 2406432678 በአሜሪካ ከሚኖሩት አባሎቻችሁ በአካል እየተገናኘን ዉይይት አካሂዷል እርዳታም እንዳደረግ ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ለምን? አንድ አትሆኑም የሚለዉ ዐማራ ድርጅቱን በሰዉ ኃይል በገንዘብ እርዳት ለማጠናከር ለአንድነት እና ለጥንካሬ ዐማራዉ በአንድ አቅጣጫ ለመሰለፍ ይበጃል በሚል እሳቤ ሁሉም የሚሰማዉን ሃሳብ ማቅረቡን እንደወንጀል አይቶ የዐማራዉን ህዝብ በጅምላ ከመኮነን እርስዎ አንድ ለመሆን የአመለካከት፣ የዓላማ እና የግብ አንድነት እንደሚያስፈልግ ወዘተ በአለዎት እምቅ እዉቀት ቢያስረዱ የተሸለ አይሆንም ነበር ብለዉ ያምናሉ?

«የደርጉ ግርፍ የሆኑትን ሌቦች» ሲሉም የሞረሽን አባላት በጀምላ ዘልፈዋል፡፡ ዶክተር ከዚህ ላይ ከእርስዎ እኔ ባላዉቅ የደርጉ ግርፍ ማለትዎ የወያኔ ግርፍ መሆንዎትን ለማሳዎቅ እና ከወያኔ ግርፍ የደርግ ግርፍ እንደሚሻል አለማወቅዎትን ለመግለጽ አስበዉ ይሆን?

ዶክተር እዉነተኛ ነኝ፣ ምሁር ነኝ፣ ታማኝ ነኝ፣ አዋቂ ነኝ፣ ወዘተ በማለት እራስዎን እየካቡ በአሉበት አስተሳሰብ ከመሬት አንስቶ በጅምላ «ሌቦች» ማለቱ የአዋቂነት መለኪያ ነዉ ብለዉ የምናሉን? የሰረቀዉ ማን? እንደሆነ የተሰረቀዉ ምን? እንደሆነ ከየት? እንደሆነ ባል ተገለጸበት የሀገራችን የወንጀል ሕግ ማንም ሰዉ በሕግ ሳይፈረድበት ሌባ ብሎ መሳደብ በሕግ እንደሚያስቀጣ በተደነገገበት፤ በጅምላ ሁሉንም ሌቦች ማለትዎ የዘረዘሩትን ማንነትዎን የሚያፈርስ መሆኑን እና በሕግ የሚያስቀጣ መሆኑን አለማወቅዎትን አይገልጽም ብለዉ ያምናሉን?

የመጽሐፍዎትን ረቂቁን አንብበዉ ገንቢ አስተያየት ሰጡኝ የአሏቸዉን አቶ በላይነህ አሻግሬ ጠበቃ እና የሕግ አማካሪ እሳቸዉ ታማኝ ነኝ በማለትዎ እሰዎን አምነዉ በእዉቀት ሳይሆን በእምነት የሠሩ መሆናቸዉን ካልሆነም የሕግ እዉቀታቸዉን የሚፈታተን መሆኑን ለአንባቢያን ግራ አጋቢ ሐሳብ እንደሆነ ከአማካሪዎት ጋር ትገነዘቡት ይሆን?

ከሁለታችሁም ሐሳብ በመነሳት አብሮ የሚሄድ አንድ የተረት አመሰራረት ላስቀምጥ። ነገሩ እንዲህ ነዉ፡፡ አንድ ማየት የተሳነዉ ሰዉ ሊወድቅ ሲንገዳገድ፣ ሌላኛዉ ማየት የተሳነዉ እንደጋገፍ ይል እና ሊደግፈዉ ሲሞክር፣ ሁለቱም ተያያዘዉ ወደቁ፣ ይህንነ በቅርብ ሲመለከት የነበረ ሰዉ፣ «እዉር ለዉር ቢደጋገፍ ተያይዞ እንዘፍ» በማለት ይናገራል፡፡ዶክተር እንዴት እንደሚያገናዝቡት «ለብልህ አይነግሩም ፣ለአንበሳ አይመትሩም፤» ነዉ እና በዚሁ አልፈዋለሁ።

ዶክተር «ካለገንዘብ ፍላጎት ሌላ ዓላማ የላቸዉም» ማለትዎ ምነዉ ስለድርጅት ምጡቅ አዋቂ እንደሆኑ አስረድተዉናል፡፡ከእሰዎ እኔ ባላዉቅም የድርጅት ሀ ሁን ለመግለጽ እሞክራሁ ድርጅት የሚለዉ ቃል ተደራጀ ከሚለዉ ግስ የተገኘ ጥሬ ዘር ነዉ፡፡ ድርጅት ለምትወደዉ ሕዝብ ችግሩን ለመፍታት የምትደርስበት መንገድ ነዉ። በመሆኑም የሚደራጀዉ እራዩን ዓላማዉን እና ግቡን ታሳቢ በማድረግ የአዘጋጀዉን መርሐ-ግብር ለማስፈጸም የተማረ የሰዉ ኃይል እና ማስፈጸሚያ ገንዘብ አስፈላጊ መሆናቸዉን የድርጅት ባለሙያ ለሆኑት ዘመናዊ ዶክተር ይሰወርበዎታል ብየ አላስብም፡፡

ዶክተር «ሞረሽ ከድርጅቱ አባላት የሰበሰበዉን ገንዘብ ሲተቹ፣ ሲወነጅሉ» እርዎእና ድርጅትዎ ገንዘብ አሰባስባችሁ እንደጠፉ በመጽሐፊዎ ገልጸዋል፡፡ታዲያ ሌላዉን በወነጀሉበት ሥራ እርስዎ ሲሠሩበት እራስዎን እና ድርጅትዎን እየወነጀሉ እና እየተቹ መሆኑን ተገንዝበውት ይሆን?

ወንጀልም የሚሆነዉ ደግሞ በድርጅት ታቅፎ፣ በአባልነት ተመዝግቦ፣ በፈቃደኝነት የሚሠጠዉን ገንዘብ ማሰባሰቡ ሳይሆን፣ ገንዘቡን ለታለመለት ዓላማ የሒሳብ አሠራርን ሥርዓትት ተከትሎ በሥራ ላይ ሳይዉል በዘፈቀደ አጥፍቶ ጠፋብኝ ማለቱ ነዉ ፡፡

ከዚህ አንጻር ቤተ-ዐማራ በነመሳፍንት እና ሰለሞን አማካይነት አወጋን የተባለዉ ድርጅት አደራጅቶ ከሞርሽ እና ከሌሎችም የሰበሰበዉን ገንዘብ በዘፈቀደ አጥፍቶ ጠፋብኝ ማለቱ እና የአደራጁትን ድርጅት ጥርት ያለ የትግል ዓላማ እና ንድፍ አልነበረዉም። የገንዘብ ብክነት ሲደርስበት ተበተነ በማለት እራሰዎን ከተጠያቂነት ለማምለጥ መሞከሩ ሌላዉ አስገራሚ ነገር ነዉ፡፡ገጽ 95

«እየወጣ ከሞነሜጨር ዉጭ ፣ምንም ዓላማ ከለለዉ ሁሉጋር አብራችሁ ካልሰራችሁ» ይሉናል

«በኛ ዘመን ተስፋን በነፍጥና በብር ልንፈጥረዉ ይገባል» ብለዋል።

1 . አሁን የአለንበት ዘመን የእርሰዎ እና የጓደኞችዎ ብቻ ነዉ ብለዉ ያምናሉ።

2 .እየወጣ ከመመሞንጭር ዉጭ ምንም ዓላማ የሌለዉ ሁሉ በማለት መጻፍን ከኮነኑ በኋላ እኔ ተስፋን በብዕር ልንፈጥረዉ ይገባል ሲሉ የሌላዉ ብዕር አለመጻፉን ለመግለጽነዉ? ወይስ እርሰዎ ከአልጻፉት በስተቀር የማይረባ መሆኑን ለማሳወቅ ነዉ?

«የቀድሞዉ ትዉልድ ተስፋን አብሮና ተባብሮ ቆርጥሞ በልቷል፤ ባዶ ሀገር፣ባዶ ካዝና፣ ባዶ ሕሊና፣ባዶ ቤት፣ ነዉ ጥሎልን የሄደዉ፤ ያትዉልድ የግራ ትዉልድ ነዉ፡፡ አስተሳሰቡ እና ስብእናዉን የገነባዉ እንደሸቀጥ በገባ ባእድ ፖለቲካዊ ባህል ነዉ» በማለት አንዱን ከአንዱ ሳይለዩ በጥቅሉ ያ ትዉልድ እያሉ ካረከሱ በኋላ፣ አንድ መስመር እንኳን ሳይሻገሩ ከዚያዉ በመቀጠል «ያለፉት ትዉልዶች ተስፋ በሌለበት ተስፋን እየፈጠሩ፣ እንዳለፉ በድርሳናት ትተዉልን አልፈዋል» በማለት እንጥፍጣፊ እምነትዎን አስፍረዋል በገጽ 4 ላይ፡፡

ዶክተር በነቀፉዎት የቀድሞዉ ትዉልድ በእምነትዎ የአለፉት ትዉልዶች በሚል ቃል ከመለየቱ በስተቀር የሐሳብ ልዩነቱን እንዴት ይረዱታል? «በአንድ እራስ ሁለት ምላስ» የሚል ፍረጃ በአንባቢዎች እንዳይሰጥዎት እመኝለዎት አለሁ፡፡

ዶር ማንነትዎን ሲገልጹ «እኔ የአማራ የብሄር አርበኛ ነኝ ፤ አምባ ገነንነትን በብእር የተፋለምኩ ወታደር ነኝ፤ የዘመኑ ፋኖ እና ጭዋ ነኝ፤ ህዝባዊ መሪ ነኝ፤ ቅን ነኝ፤ እዉነተኛ ነኝ ፤ታማኝ ነኝ፤ ሩቁን ተገንዛቢ ነኝ፤ ምሁር ነኝ፤ ብርቱ ነኝ፤ በማለት «ለራስ ሲቆርሱ አያስንሱ» ሲሉ አባቶቻችን የነገሩንን ወርቃማ ቃል ለራሰዎ ምስክርነት ሰጥተዋል። ተመልካችና ታዛቢ የሚለው ደግሞ በተቃራኒዉ ከመሆኑም በላይ፣ በራሰዎ ብዕር ገጽ 8 ላይ የዚህን ተቃራኒ ብዙ ብለዋል።

ዶክተር ከሕግ አንፃር አንድ ሰዉ ይህ ነገር የኔነዉ ብሎ ቢጠይቅ፣ የአንተ ለመሆኑ ማስረጃ አቅርብ እንደሚባለዉ ሁሉ፣ እርስዎም ነኝ ለሚሉት ሁሉ ከእርስዎ ዉጭ ማስረጃ ማቅረብ አይጠበቅብኝም ይሉን ይሆን? ሆንኩ እና ሠራሁ ለሚሉት ሁሉ ከራስዎ ዉጭ የሚመሰክርልዎ ሥራዎት እና ሥራዎትን የሚያዉቁ ቢሆኑ የተሸለ አይሆንም ነበር ብለዉ ያስባሉ?

ዶክተር ሕዝባዊ መሪ ነኝ ብለዋል፡፡ የሕዝብ መሪ ለመሆን መንገዱ አንድም በአምባገነንነት ካልሆነም በሕዝብ ምርጫ ነዉ፡፡እርስዎ ግን በህልምዎ ካልሆነ በእዉን መሪ እንዳልሆኑ አገር ያወቀዉ ፀሐይ የሞቀዉ ነዉ፡፡ «ድሀ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ፣ንጣቱ ይገድለዉ ነበር» ስለሚባል እንዳሉት እንዲሆንለዎት ከመመኘት ባሻገር፣ ለእርስዎ የማይጥመዎት በመሆኑ በዚሁ አልፈዋለሁ፡፡

ዶክተር ስለራስዎ ያላተናገሩት ስለሌለ በጽሑፈዎ ሕዝቤ የሚል ቃል ደጋግመው ተጠቅመዋል። አንድ ሰዉ ሕዝቤ ብሎ ለመናገር ለሕዝብ የአለዉን አቋም በመርሐ ግብር አስፍሮ ከአቻ ድርጅት ጋር ተወዳድሮ፣ የሐሳብ እሸናፊነትን አግኝቶ፣ በብዙሃን ድምፅ የተመረጠ ሰዉ የሚናገረዉ እንጂ፣ ተስፈኛ የሆነ ሰዉ እንዳል ሆነ እስካአሁንም ባለማወቅዎት አንባቢያን ምን እንደሚለዎት ፈጣሪየ ይወቅ ፡፡

ጎንደር ዩንቨርሲቲ አንትሮፖሎጂ ፣ታሪክን፣ ቋንቋዉን፣ ባህሉን፣ሃይማኖቱን፣ ፖለቲካዉን፣ ኢኮኖሚዉን ፣ባህርዩን ፣ልምዱን፣ ትዉፊቱን፣ አደረጃጀትን፣ ወዘተ ማጥናትዎትን ነግረዉናል። (ገጽ 8) ከእርሰዎ ጽሑፍ ጋር አብሮ የሚሄድ አንድ ነገር ላንሳ።

አንድ ሰዉ ለጓደኛዉ የአባቴ ቤት አስር ደጃፍ አለዉ ሲለዉ፣ በልተወዉ አልተገደገደም በለኛ አለዉ ይባላል፡፡እርስዎ ይህን ሁሉ ከአጠኑ የቤቱ የደጃፍ ብዛት ዓይነት ሊሆን አይችልም ይላሉን?

ዶክተር ከእስዎ እኔ ባላዉቅ መማር የራስን ሰዉ መሆን ተገንዝቦ የሌላዉን ሰዉ መሆን ማገናዘብ የሚያስችል ፣ለራሱ የሚያስበዉን ለሌላዉም ማሰብ የሚያስችል፣ የዘመናዊ ዲሞክራሲ ጽንሰ ሐሳብ የተመሠረተዉ በነገድ ማንነት ላይ ሳይሆን፣ በግለሰብ ነፃነት እና በምርጫ መሆኑን የሚያሰገነዝብ፣ አንድ ግለሰብ የፖለቲካ ነፃነቱን የዜግነት መብቱን የሚቀዳጀዉ በነገዱ አማካይነት ሳይሆን፣ እራሱ ነፃ ሰዉ ሁኖ የሚፈልገዉን መምረጥ ሲችል ብቻ መሆኑን የሚያሳዉቅ፣ ለስኬታማ ዉጤት አስፈላጊ ነገሮች አዕምሮታዊ ስሜታዊ እና መንፈሳዊ ጤንነቶች መሟላት መሆናቸዉን ማወቅ የሚያስችል ግንዛቤ ማዳበር መሆኑን ይዘነጉታል አልልም። መማር ብቻዉን ኅሊና ከለለዉ የማይሠራ በመሆኑ እዉቀትን የሚመራ ኅሊና አስፈላጊ መሆነን፣ ከሁሉም በላይ ጥሩ መንገድ ለራስ የሚያስበዉን ለሌላዉም ማሰብ ሲቻል መሆኑን የሚያሳዉቅ ነዉ፡፡

አንድ የቄስ ተማሪ ተስፋዉ እና ቀለቡ ተስካር ስለነበር ፣ሀብታም ሲሞት ሆዱ እሰኪሞላ እንደሚበላ ተስፋ አድርጎ ሳለ፣ አንድ ሀብታም ሞቶ ከተስካሩ እንዳሰበዉ ሳያገኝ ቀረ፡፡እናም «እንደሞትዎ ደስ ብሎኝ፣ እንደ ተስካርዎ ከፋኝ» አለ ይባላል፡፡

እኔም እንደ ተማሪዉ አርቆ በመማር ተስፋ ስለነበረኝ እንደመማርዎ ደስ ብሎኝ ፣እንደ መጽሐፍዎ ባይከፋኝም አላስደሰተኝም፡፡

ሙላት በላይ